# የወቅት አጋማሽ የአየር ጠባይ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1 እስከ ከኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እና በቀሪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ እና ምክረ ሃሳብ

ዲሴምበር 2022
አዲስ አበባ

ማስታወሻ

እባክዎ http://www.ethiomet.gov.et ይጎብኙ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|


እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ የበጋ ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ ........ 1

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ........ 2

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 4

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ 5

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2022 ድረስ የነበረው ........ 6

የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 6

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 7

ካርታ 4ሀ ፡ የኦክቶበር ወር 2022 የእርጥበት ሁኔታ ........ 8

ካርታ 4ለ፡ የኖቬምበር ወር 2022 የእርጥበት ሁኔታ ........ 8

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 8

ካርታ5ሀ፡በኦክቶበር ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን ........ 9

ካርታ 5ለ፡በኖቬምበር ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን ........ 9

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 9

ካርታ 6ሀ በኦክቶበር ወር ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች ........ 10

ካርታ 6ለ. በኖቬምበር ወር ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች ........ 10

ካርታ 6ሐ. በኦክቶበር ወር ለሰውል ልጅ ለመኖር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች ........ 10

ካርታ 6መ. በኖቮምበር ወር ለሰው ልጅ ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች ........ 10

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2022 እስከ ጃንዋሪ 31/2023 የሚኖረው ........ 11

የአየር ጠባይ አዝማሚያ ........ 11

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2022 እስከ ጃንዋሪ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 12

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2022 እስከ ጃንዋሪ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 13

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2022 እስከ ጃንዋሪ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 13

# ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ የበጋ ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

## አጠቃላይ

የዘንድሮው በጋ የአየር ጠባይ ትንበያ በተሰጠበት ወቅት የትሮፒካል ፓስፊክ ምስራቃዊና መካከለኛዉ ክፍሎች የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛው በታች የመቀዝቀዝ ሁኔታ ከመደበኛው በታች በመቀዝቀዝ (ENSO-La Nina) ሆኖ የመቀጠል እድሉ 70-80% ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ ተወስዷል:: በተጨማሪም የሰሜናዊ ህንድ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ (Near-neutral IOD) ሁኔታ ቢኖርም፤ በበጋ ወራቶች ላይ ወደ negative IOD ተፅእኖ ሥር ሊሆን እንደሚችል በመጠበቁና ይህም ሁኔታ የከባቢው አየር (Atmospheric conditions) በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የበጋው ደረቅ፤ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ እንዲሚያመዝን የተተነበየ ሲሆን፤ እንዲሁም ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመደበኛው በታች ዝናብ እንዲኖር ሊያደርግ እንደሚችል መጠቆሙ ይታወሳል። በዚህ መሰረት ባለፉት የበጋዉ ሁለት ወራት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ የአየር ጠባይ ተፅእኖ ስር ቆይተዋል፡፡

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ባለፉት ሁለት የበጋ ወራት የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ ወራት ሊኖር የሚችለው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በግብርና፣ በዉሃ እና በጤና ሴክተሮች ላይ አሳድሮ የነበረው አዎንታዊ እና አሉታዊ ተፅዕኖ ዳሰሳ እንዲሁም በቀጣዮቹ ሁለት ወራት ሊያሳድር በሚችለው ተፅእኖ ላይ ጽሁፍ ይቀርባል።

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፉት የበጋ ሁለት ወራት (ከኦክቶበር እስከ ኖቬምበር) 2022 አብዛኛዉን ጊዜ ደረቃማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስተዋለ ቢሆንም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብ ኦሮሚያና የደቡብ ሶማሌ፣ በተጨማሪም የመካከለኛው ኦሮሚያ፣ በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፤ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍልች ሊይ ከነበራቸው የደመና ሽፋን ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያላው ዝናብ አግኝተዋል። በተጨማሪም የኦክቶበር ሁለተኛዉ አስር ቀናት እንዲሁም በኖቬምበር መጀመሪያዉ አስር ቀናት ከተጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት እርጥበታማዉ አየር ወደ ሀገራችን እንዲገባና በተለይም በምዕራብ አጋማሽና ደቡብ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ የነበረዉ ደመና ጠንካራ እና አልፎ አልፎ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የማስከተል አቅም ነበረዉ፡፡ በመሆኑም በምዕራብ አማራ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በምዕራብና ደቡብ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵእና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ አንዳንዶቹን ለመጥቀስም በጎሬ 34.0፣ በነቀምት 39.8 እና 32.5፣ በአማን 66.1፣ በበደሌ 34፣ በቡሬ 64፣ 45.0፣ በቦሬ 34፣ በቻግኒ 42.4፣ በጨፋ 42.4፣ በዳንግላ 51.5፣ በጊዮን 32.2፣ በጊዳአያና 63.3፣ 36.2፣ 46.1 እና 64፣ በጉንዶመስቀል 34፣ በእምድብር 36፣ በኮንሶ 34.8፣ በላሬ 45፣ በሊሙገነት 46.7፣42.0፣ 38.5 እና 38.8፣ በማሻ 36.4፣ 40.2፣ 30.6፣ እና 56.4 በነጆ 40.5፣ 36.0 እና 38፣ በሸርቆሌ 36.2፣ በሰኮሩ 50.5፣ በቴፒ 31.3 እንዱሁም በተርጫ 54፣ በአቦቦ 30.4፣ በአይራ 33.2፣ በአርጆ 36.4፣ በአይከል 32.7፣ በቡርጂ 30.6፣ በቻግኒ 55.6፣ በዶሎመና 68.5፣ በጋምቤላ 34.0፣ በጊኒር 30.0፣ በጂንካ 37.9 ፣ በሻምቡ 31.2 እና በወላይታ ሶዶ 50.5 በአርባ ምንጭ 41.7፣ በአይከል 46.3፣ በባህር ዳር 35.8፣ በሀገረማርያም 46.7 እንዲሁም በቀብሪዳሀር 50.2 በቁሉምሳ 95.7 እና 32.6፣ በጎዴ 30.1 በሚሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፈዉ የበጋ ወቅት አጋማሽ (ከኦክቶበር እስከ ኖቨምበር) 2022 የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ በአገዉ አዊ፣ በጋምቤላ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ሁሉም ዞኖች፣ በቄለም፣ በምዕራብ፣ በምስራቅና ሆሮጉዱሩ በወለጋ፣ በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በአርሲና ባሌ፣ በጉጂና ቦረና፣ በሲዳማ ክልል ዞኖች፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሁሉም ዞኖች፣ በሊበን በአፍዴር፣ በሸበሌ፣ በኖጎብና በቆራሂ ጀረር ዞኖች ላይ ከ50-400 ሚሜ የሚደርስ ከ5-39 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በትግራይ ክልል ዞኖች፣ በዋግህምራ፣ በኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ በምስራቅና ምዕራብ

ሐረርጌ፣ በአፋር ክልል ሁሉም ዞኖች እና በፋፈን ዞን ላይ ከ10-50 ሚሜ የሚደርስ ከ10 ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ፡፡


ባለፈዉ የበጋ ወቅት አጋማሽ (ኦክቶበር እስከ ኖቬምበር) 2022 የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦችና ሲዳማ ክልል ከሞላ ጎደል ሁሉም ዞኖች፣ በቄለም ወለጋ፣ በሆሮጉዱሩ፣ በምዕራብና ምስራቅ ወለጋ ዞኖች፣ በኢሊባቦር፣ በምዕራብ አርሲ፣ በሊበን፣ በአፍዴር፣ በሸበሌ፣ በዶሎ፣ በቆራሄ ጃረር፣ በጥቂት ኖጎብና ደገሃቡር ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡

በአጠቃላይ የበጋው ወቅት አጋማሽ ማለትም በኦክቶበርና በኖቬምበር ወራት የዘነበው የዝናብ መጠን በምዕራብና ደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋ ዝናብ እንደነበረና በመጠን ረገድም ከ10-400 ሚሜ የሚደርስ ዝናብ እንደተመዘገበ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሁለቱ ወራት ከሚጠበቀዉ መደበኛው የዝናብ መጠን ጋር ሲነጻጸር በቤንሻንጉል ጉሙዝና አጎራባች በሆኑት የምዕራብ አማራ ኪስ ቦታዎች፣ በምዕራብና ደቡብ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላና በሱማሌ ደቡባዊ አጋማሽ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ ተስተውሏል፡፡ በአጠቃላይ በጋ ወቅት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች በአመዛኙ መደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1፣2 እና 3)፡፡ በሌላ በኩል በተለይም በሀገሪቱ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከጊዜ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ ተስተውሏል፡፡


ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የበጋ ሁለት ወራት (ከኦክቶበር እስከ ኖቬምበር) 2022 አብዛኛዉን ጊዜ ደረቃማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖ እንደነበረ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሂዱ በአንዳንድ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ እንደነበረ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በአንፃሩም ከደረቃማዉ የአየር ሁኔታና ከደመና ሽፋን መሳሳት ጋር ተዳምሮ በአብዛኛዉ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የማለዳውና የሌሊቱ ቅዝቃዜ በአንፃራዊ ሁኔታ ተጠናክሮ እንደነበረ መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን፣ በተለይም በአንዳንድ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በተከታታይ ቀናት ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ፡፡ ይሁን እንጂ ለእርጥበት መጨመር ምቹ ከነበረው የሚቲዎሮሎጂ ክስተት መጠናከር ጋር ተያይዞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብ ኦሮሚያና የደቡብ ሶማሌ በተጨማሪም የመካከለኛው ኦሮሚያ፣ በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን የሚደርስ የእርጥበት ይዘት እንደነበራቸው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም ተጠናክሮ የታየው እርጥበታማ ሁኔታ እድገታቸውን ላልጨረሱና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች እድገት የሚያስፈልጋቸውን እርጥበት ከማስገኘት አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበርው። በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የአርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተለያዩ የግብርና እንቅስቃሴዎችን እንዲያከናውኑ አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን፣ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልም አዎንታዊ ሚና ነበረው። በተጨማሪም የኦክቶበር ሁለተኛዉ አስር ቀናት እንዲሁም በኖቬምበር የመጀመሪያዉ አስር ቀናት በተለይም በምዕራብ ኢጋማሽና በደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የነበረዉ ደመና ጠንካራ እና አልፎ አልፎ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የማስከተል አቅም ነበረዉ፡፡ ይህንንም ተከትሎ የነበረው ከባድ ዝናብ ሙሉ ለሙሉ ባልደረሱና በአንዳንድ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ የመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች የተገኘው እርጥበት የጎላ ጠቀሜታ የነበረው ሲሆን፣ በአንጻሩም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተገኘዉ እርጥበት በደጋማው አካባቢ ለተዘሩ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት እንዲሁም ውሃ አጠር ለሆኑ አካባቢዎች ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማቸት ጥሩ አጋጣሚን የፈጠረ ነበር (ካርታ 4ሀ)፡፡


ካርታ 4ሀ ፡ የኦክቶበር ወር 2022 የእርጥበት ሁኔታ


ካርታ 4ለ፡ የኖቬምበር ወር 2022 የእርጥበት ሁኔታ





## ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ሁለት የበጋ ወራት (ከኦክቶብር 1 እስከ ኖቬምበር 30) የነበረው የአየር ጠባይ በዉሀዉ ዘርፍ ስንመለከት በኦክቶበር ወር የነበረው የአየር ሁኔታ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በደቡብ እና በምዕራባዊ የሀገሪቱ አጋማሽ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት መጠን እንደነበራቸው መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ አብዛኛው ገናሌ ዳዋ፣ ኦሞ ጊቤ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣የመካከለኛው እና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የመካከለኛው ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም በጥቂት የመካከለኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም በጥቂት የላይኛው አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ተከዜ፣ የላይኛው እና የታችኛው ዋቤ ሸበሌ፣ በጥቂት የታችኛው ባሮ አኮቦ እና ገናሌ ዳዋ እንዲሁም ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ሲሆኑ የተቀሩት ተፋሰሶች ግን በበጋ ወቅት ደረቃማ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ፡፡ በተጨማሪም በኖሸምበር ወር በኖሸምበር ወር በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ የነበረ ሲሆን፤ ሆኖም በጥቂት ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ነበራቸው። ለአብነትም በላይኛው እና በመካከለኛው ባሮ አኮቦ እና በጥቂት ታችኛው አሞ ጊቤ ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ በመካከለኛው አባይ፣ በመካከለኛው እና ታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛው እና መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው ዋቤ ሸበሌ፣ በጥቂት የላይኛው ገናሌ ዳዋ እንዲሁም ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ነበራቸው፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች በአብዛኛው ቦታዎቻቸው ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5ሀ እና 5ለ) ፡፡





ካርታ5ሀ፡በኦክቶበር ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን


ካርታ 5ለ፡በኖቬምበር ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን

## ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


በኦክቶበር 2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ለወባ መራባትና ስርጭት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ ቦታዎች የሰሜን ምዕራብና ምዕራብ፣ በምስራቅ እና በመካከለኛው ደቡብ ማለትም ሰሜን ጎንደር፣አዊ፣ባህር ዳር ዙሪያ፣ ምዕራብ ጎጃም፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ቶንጎ፣ ካማሽ፣ ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ጉጂ፣ ሸካ፣ከፋ፣ ቤንች ማጅ፣ ወላይታ፣ባስኬቶ፣ ጌዲዮ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ሲዳማ፣ ሁሉም የጋምቤላ ዞኖች፣ ቆራሂ፣ ደጋሀቡር እና ዋርደር ለወባ መራባት ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች ሲሆኑ፤ በሌላ በኩል በዚህ ወር በአንድ አካባቢ ለሰው ልጅ ለመኖር ተስማሚ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች ስንመለከት አብዛኛው የሀገሪቱ ከፍተኛና መካከለኛ ቦታዎች ምቹና መካከለኛ ምቹ (THI 14-26) የነበሩ ሲሆኑ የሀገሪቱ ሰሜናዊ ደቡባዊ በጣም ከፍተኛ ቦታዎች በጣም ቅዝቃዜ (THI<14) የሆነ የአየር ሁኔታ እንደነበራቸው ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ የምስራቅ እና የምዕራብ በጣም ዝቅተኛ ቦታዎች ሞቃታማ(ምቹ ያልሆነ, THI>26) የአየር ሁኔታ እንደነበራቸው መረጃዎች ያሳያሉ ((ካርታ 6ሀ እና 6ለ)።

በኖቨምበር 2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ለወባ መራባትና ስርጭት ከኦክቶበር ወር የቀነሰ ቢሆንም በኦክቶበር ወር ላይ የነበረው ምቹ ሁኔታ የወባ ትንኟ ለብዙ ጊዜ እንድትኖር ጥሩ ሁኔታ ስለሚፈጥርላት በኖቨምበርና በቀጣዩቹ ወራቶች ትንኟ የመኖር እድሏ ከፍ ያለ እንደሚሆን ይጠበቃል፤ በዚህ መሰረት በኖቨምበር ወር ላይ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍል ላይ ማለትም ኢሊባቦር፣ ሰሜን ጅማ፣ ሸካ፣ ቤንች ማጅ፣ ደቡብ ኦሞ፣ የጋምቤላ (ጎደሬ እና ዞን 2) ለወባ መራባት ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች ሲሆኑ፤ በሌላ በኩል በዚህ ወር በአንድ አካባቢ


ለሰው ልጅ ለመኖር ተስማሚ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች ስንመለከት አብዛኛው የሀገሪቱ ከፍተኛና መካከለኛ ቦታዎች ምቹና መካከለኛ ምቹ(THI 14-26) የነበሩ ሲሆኑ የአገሪቱ ሰሜናዊ እና ደቡባዊ በጣም ከፍተኛ ቦታዎች በጣም ቀዝቃዛ (THI<14) የሆነ የአየር ሁኔታ እንደነበራቸው ስንመለከት በሌላ በኩል ደግሞ የሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅና እና የምዕራብ በጣም ዝቅተኛ ቦታዎች ሞቃታማ(ምቹ ያልሆነ, THI>26) የአየር ሁኔታ እንደነበራቸው መረጃዎች ያሳያሉ ((ካርታ 6ሐ እና 6መ)።





ካርታ 6ሀ. በኦክቶበር ወር ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች




ካርታ 6ለ በኖቨምበር ወር ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች




ካርታ 6ሐ. በኦክቶበር ለሰው ልጅ ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች




ካርታ 6መ. በኖቨምበር ወር ለሰውል ልጅ ለመኖር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች


# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2022 እስከ ጃንዋሪ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የዲሴምበር እና የጃንዋሪ ወራቶች በአብዛኛው የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ ገፅታዎች የሆኑት ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝኑበት ከመሆኑም በተጨማሪ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በተለይም ለውርጭ ተጋላጭ በሆኑ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሚያይልበት ጊዜ ነው። በአንፃሩ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ እንዲሁም ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞም በጥቂት የሰሜን ምሥራቅ አማራ ቦታዎች ላይ ዝናብ ይስተዋላል።

በመጪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ አብዛኛው ክፍል የባህር ወለል ሙቀት እየጨመረ እንደሚገኝ የሚስተዋል ቢሆንም፤ በቀሪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት እ.ኤ.አ 2022-23 (ዲሴምበር እና ጃንዋሪ) ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት ከታህሳስ ወር በኋላ ቀስ በቀስ ሙቀቱ ወደ (Enso-neutral) የመሆን እድሉ እስከ 60% ሊደርስ እንደሚችልና እንዲሁም የህንድ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ (Neutral_IOD) ሆኖ እንደሚቀጥል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

<u>በመሆኑም አሁን ከሚስተዋለውና ለመጪዎቹ ሁለት ወራት ከተተነተኑ የባህር ወለል ሙቀትና የከባቢ አየር ሁኔታዎች በመነሳት በአብዛኛው የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝን ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በአንዳንድ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ እንደሚጨምር ይጠበቃል።</u>

<u>በዚሁም መሰረት ከኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ኦሮሚያ ዞኖች ከሆኑት የቄለም ወለጋ፣ የጅማና የኢሉባቦር ዞኖች፤ የደቡብ ብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፤የሲዳማ ክልል፤ የደቡብ አጋማሽ የሶማሌ ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ከዚህም ሌላ የበጋው ወቅት ማብቂያ አካባቢ ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ በምሥራቅ አማራ የሚገኙ የሰሜን ሸዋ፣ የሰሜንና  የደቡብ ወሎ ዞኖች ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል።</u>




ካርታ 7. ከታህሳስ እስከ ጥር 2023 ሊኖር የሚችለው የዝናብ ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2022 እስከ ጃንዋሪ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ የበጋ ወራት በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቅ የአየር ሁኔታ የሚጠበቅ ሲሆንና ይህም ሁኔታ የደረሱ የመኸር ሰብሎችን ለመሰብሰብና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ ስለሆንም አርሶ አደሮች ይህንኑ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም በማሳ ላይ የሚገኙና የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ እንዲያነሱ ይመከራሉ፡፡ በአንጻሩ ከደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ በሆኑ የሀገሪቱ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ ከቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን የተነሳ በሌሊትና በማለዳ ሊስተዋል የሚችለው ቅዝቃዜ በእንሰሳትም ጤናም ሆነ በመስኖ በመታገዝ ለሚለሙ አትክልቶች፣ የፍራፍሬ ተክሎች እንዲሁም በቋሚ ተክሎች አጠቃላይ እድገታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚኖረዉ የሚመለከታቸዉ አካላት ከወዲሁ አስፈላጊውን ዝግጅትና ጥንቃቄ እንድያደረጉ ይመከራል፡፡ በሌላ በኩል ከኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ኦሮሚያ ዞኖች የሆኑት የቄለም ወለጋ፤የጅማና የኢሉባቦር ዞኖች፤ የደቡብ ብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ የሲዳማ ክልል፤ የደቡብ አጋማሽ የሶማሌ ዞኖች በአብዛኛው

ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ እርጥበት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ይህም የሚጠበቀው እርጥበት በአካባቢው ለሚገኙ ቋሚ ተክሎች፣ ለግጦሽ ሣርና ውሃ አቅርቦት የተወሰነ አስተዋጽዖ ከመኖሩም በተጨማሪ የበጋው ወቅት ማብቂያ አካባቢ ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ በምሥራቅ አማራ የሚገኙ የሰሜን ሸዋ፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች ሊያገኙ የሚችሉት ቀላል መጠን ያለው እርጥበት የበልግ ወቅት የእርሻ እንቅስቃሴን ቀድመው ለሚጀምሩት ከላይ በትንበያው ለተገለፁት አካባቢዎች ለሚካሄደው ለማሳ ዝግጅትና ለዘር ወቅት የእርሻ እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል ፡፡

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2022 እስከ ጃንዋሪ 31/2023_የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀሪዎቹ የበጋ ወራት  በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፤ በሌላ በኩል በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ እንዲሁም በጥቂት የሰሜን ምሥራቅ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ይህንን ሁኔታ ተከትሎ የመካከለኛው እና የታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ የመካከለኛው ዋቤ ሸበሌ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ባሮ አኮቦ እንዲሁም የመካከለኛውና እና የታችኛው አባይ ተፋሰሶች ሲሆኑ፤ የተቀሩት የሰሜን፣ ሰሜን ምስራቅ እንዲሁም መካከለኛው ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል፡፡

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2022 እስከ ጃንዋሪ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀሪዎቹ የበጋ  ሁለት ወራት የወባ ትንኟ በአንድ አካባቢ የመኖር እድሏ ከፍ ያለ ስለሚሆን፤ በእነዚህ ወራቶች ምቹ በነበረባቸው ቦታዎች የወባ በሽታ ስርጭት ጨምሮ ሊቀጥል ስልሚችል ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። በዚሁ መሠረት በምንጠቀምባቸው መስፈርቶችን  መሠረት በማድረግ የተመረጡ አናሎግ አመታቶች (2010/11፣ 2007/08 እና 2021/22)ንየነበራቸው መረጃ እንደሚያሳየው የደቡብ ምዕራብ ጥቂት ቦታዎች ማለትም ሸካ፣ ከፋ እና የጋምቤላ ጎደሬ ዞን ለወባ መራባት ምቹ የአየር ሁኔታ የሚኖራቸው ቦታዎች እንደሆኑ መረጃዎች ስለሚጠቁሙ እና እንዲሁም አጠቃላይ የበጋውን ምቹ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለወባ መፈጠርና መስፋፋት ምቹ የአየር ሁኔታ ሊፈጠር የሚችሉ ሁኔታዎችን በማፅዳት ህብረተሰቡ ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል በቀጣይ ሁለት ወራቶች የሀገሪቱ ከፍተኛ ቦታዎች ማለትም የሰሜን፣ የደቡብ፣ የምስራቅ እና የመካከለኛው ከፍተኛ ቦታዎች ላይ የለሊትና የማለዳ ቅዝቃዜ ሊጨምር (THI<14) ስለሚችል ለብርድ ተጋላጭ ከመሆን የሚከላከሉ ነገሮችን ህብረተሰቡ እንዲጠቀምና ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደረግ እንመክራለን።